# Migration Industry Ethiopia

Migrating out of Poverty

## የጥናት አጀንዳ

በአንድ የግለሰብ የስደት ሂደት ውስጥ ብዙ የድርጊት ተሳታፊዎች ማለትም የተለያዩ ማህበራዊ መረቦች፣ ደላሎች፣ የድንበር ተቆጣጣሪ ኤጀንቶች፣ የስልጠናና ሰረቲፊኬት ተቋማት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሀይማኖት ድርጅቶች ተካፋይ ናቸው፡፡ እነዚህ የድርጊት ተካፋይ አካላት በጥቅሉ "የስደት እንደስትሪ" ተብለው ይጠራሉ፡፡ ይህ የጥናት ፕሮጀክት የስደት እንደስትሪውአካላት በስደት አሠራር ፤ በስደት ጉዞና በግብይቱ ሂደትን በማሟላት በኩል ያላቸውን ሚና በጾታ፣ በትውልድና በብሄር አንጻር በመከፋፈልና በመመርመር ያለንን ግንዛቤ ያሳድጋል፡፡ ስደተኝነትን ለማሳካት የሚረዱ መሠረተልማቶችን በተመለከተ የሚናገኘው የተሻለ ግንዛቤ የስደተኞች ብዝበዛ ለመቀነስና ከስደት የሚገኙ ጥቅማጥቅሞች ለማሳደግ የሚረዱ ምክረ-ሀሳቦችብ ለመስጠት ይረዳናል፡፡

## መሠረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች

- የስደት ድለላ ጾታን፣ ብሄርን ዕድሜንና የስደተኛ ፍሰትን ቅርጽ ማስያዝንና በቤተሰብ ውስጥ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ እንዴት የጣምራል?
- ደላሎችና የግል አሰቀጣሪ ኤጀንሲዎች የኢትዮጵያ ወንዶችና ሴቶች ሠራተኞችን ወደ መካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች፤ ወደ የደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊከና አውሮፓ የሚመለምሉት፣ የሚያጓጉዙትና የሚያሰማሩት እንዴት ነው?
- የስደት እንደስትሪ አካላት ከኢትዮጵያ ወደ መካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች፤ ወደ የደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊከና አውሮፓ የሚደረግ የመሬት የስደት ጉዞን የሚያዘጋጁት እንዴት ነው?
- በደላሎችና በስደተኞች መካከል ያሉት ማህበራዊና ባህላዊ መስተጋብሮች ምንድን ናቸው፤ ሀይልና ቁጥጥርን እንዴት ይጋራሉ; እነዚህ ንገሮች ከጾታ፣ከዘርና እድሜ አንጻር እንዴት ተጽዕኖ ያስከትላሉ?

## የጥናቱ አላማዎች

- የተወሰኑ የስደት እንደስትሪ አካላት ኢትዮጵያዊያን ስደተኛ ሠራተኞችን በመመልመል፣በማጓጓዝና በመመደብ ወደ መካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች እንድሁም ወደ የደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክና አውሮፓ የመሬት ላይ ቅደምተከተል ጉዞ ረገድ እንዴት እንዴሚሳተፉ ጾታን፣ ብሄን፣ ትውልድንና የሃይል ግኑኝነት በመውሰድ ስደትን በማመቻቸትና በመቆጣጠር በሚሳታፉ አካላት መካከል ያሉትን ግኑኝነቶች መመርመር
- ከኢትዮጰጵያ የስደት ጉዞ መነሻዎች ጀምሮ እስከ የመንግስታት ድንበር መሻገር ባሉት ሂደቶች ውስጥ የስደት እንደስትሪ ሚና ምን እንደሆነ መመርመር
- የስደት ድለላና የድብቅ ጉዞ ልምምዶች የሚፈጠሩበት ሁኔታና ስደተኞች የላቸውን የቁሳቁስና የገንዘብ ሀብት በሥራ ላይ በማዋል ረገድ የላቸውን የጋራ ልምድ እንዲሁም ወደ መካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች፤ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊከና አውሮፓ የሚደረገውን አደገኛ ጉዞን በተመለከተ ያላቸውን አውቀት ማሳየት
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ኤጀንሲዎችና ደላሎች የመሳሰሉት የስደት ሂደቶችን በማቀድ በማሰተዋወቅና በማደራጀት ሥራ ላይ እንድሳተፉ የሚያደርግ የማህበራዊ-ፖለቲካና ምጣኔ ሀብታዊ እሳቤዎችን መመርመር

## የዚህ ጥናት ፕሮጀክት እምቅ አስተዋጽዖዎች

የዚህ ጥናት ግብ በየደረጃው በስደተነኞች ላይ የሚደርሱትን ብዝበዛዎች፣ ሽፍጦችና ማጭበርበሮችን በነዚህ ሂደቶች ውስጥም የደላሎች ሚና መለየት ብቻ ሳይሆን በስደተኝነት ሂደት ውስጥ ስደተኞችን ከመሸጋገሪያ ጣቢያዎች ጋር በማላመድና ሌሎች እርዳታዎችን ለመሳሌ በተለያየ ስደት ሂደት ውስጥ የሥራ እድል እንዲየገኙ በማድረግ ረገድ የደላሎች የሚጫወቱትን ሚና ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የገንዘብ ዝውውርንና በዚህ ሂደት ውስጥ የስደት አገናኞችን ሚና መከታተልን አላማው የደርጋል፤ እንዲሁም ከስደተኞች አመለካከት አንጻር የድለላን ልዶች ይዘግባል፡፡ በጥናቱ የሚሰበሰቡ ሁሉም መረጃዎች በጾታ፣ በትውልድና በሄር ተለይተው ይጠናቀራሉ፡፡ የዚህ ጥናት ግኝቶች ስደትን በተመለከተ ፖሊሲና ተግባራዊ ሥራዎችን ለሚሠሩት ለኢትዮጵያ መንግስትና ለሌሎች በስደት ጉዳዮች ላይ ለሚሠሩ ብሄራዊና አህጉራዊ ድርጅቶች የሀሳብ ግብአት ይሰጣል፡፡

Organisation for Social Science Research in Eastern and Southern Africa (OSSREA)
Research Lead - Dr. Fekadu Adugna
Email - info@ossrea.net
www.ossrea.net
migratingoutofpoverty.dfid.gov.uk
+251-11-1239484, P.O. Box 31971, Addis Ababa, Ethiopia

UKaid from the British people